# አገር እንዴት ሰነበተች ቁጥር 29

ነሐሴ 29 ቀን 2014 ዓም(04-09-2022)

ባሳለፍናቸው የአገር እንዴት ሰነበተች ቅንብሮቻችን ያልነካነውና ያላነሳነው የአገራችን ጉዳይ የለም። በሁሉም ዝግጅቶቻችን ያቀረብናቸው ትንተናዎችና ትችቶች ጥላቻ የወለዳቸው ሳይሆኑ በመረጃ የተረጋገጡ ለመሆናቸው አድማጭ ከሚያዬው ሃቅ ጋር አመዛዝኖ ፍርዱን እንደሚሰጥባቸው እርግጠኞች ነን።ዓላማችን የሌለና ያልሆነ ልብ ወለድ ወሬ በመንዛት አድማጮቻችንን ለማሸበርና ያገራችንን ገጽ ለማጠልሸት እንዳልሆነ ሁሉም ከእውነት ጋር ያልተጣላ ይመሰክረዋል ብለን እናምናለን።የዛሬውም ዝግጅታችንም ያንኑ ነባር ዓላማችንን የተከተለና ላገራችንና ለሕዝቡ የሚበጀውን ለመጠቆም ካለን ጽኑ እምነት የተነሳ እንጂ አሉቧልት ለመንዛት የሚደረግ እኩይ ዓላማ የሰነቀና ካገር አፍራሾቹ ተርታ የሚያሰልፈን አይሆንም።

በአገር አፍራሾቹ ተርታ መሰለፍ ማለት ከነሰኞቹ ሥርዓት ጋር ቆሞ ሕዝቡን በማወናበድና የአፍራሽ ሃይሉን ወንጀል በመደበቅ አገርን ለመበታተን የተዘጋጀውን መርዘኛ የፖለቲካ ሴራ ሽፋን በመስጠት ለአገር አንድነት፣ለሰላም፣ ለዕድገት፣ለእኩልነትና ፍትሕ የቆመ ነው በማለት በተከፈላቸው ሂሳብና ጥቅም ልክ በመጮህ የሚያወናብዱ ይሉኝታ ቢስ ጋዜጠኞችና የዜና ዘጋቢዎች መሆን ማለት ነው። እኛና እኛን መሰሎቹ አገር ወዳዶች ግን ከዚህ አይነቱ ወራዳ ተግባር የራቅን ለመሆናችን ሥራችን ይመሰክራል።ለሥርዓቱና ለደጋፊዎቹ ምንም አይነት ሃዘኔታና የመታለል ድክመት አይኖረንም።አካፋን አካፋ ከማለት ሸብረክ አንልም።በመሬት ላይ ያለውንም ገሃድ ከመግለጽ ወደኋላ አንልም።

የእኛን አቋም ካስረዳን በኋላ በዚሁ አቋማችን የምናቀርበው የዛሬው ቁጥር 29 ቅንብራችን እንዳለፉት ሁሉ የሰሞኑን ያገራችንን ሁኔታዎች በግልጽ የምንዳስስበት ይሆናል።

ባለፈው ሳምንት ያቀረብነው በአገራችን ሰማይ ላይ ተንጠልጥሎ የነበረው የጦርነት ድባብ በተግባር ተገልጾ አድማሱን እያሰፋ ለብዙ ዜጎች ሞትና መፈናቀል ምክንያት ሆኗል።በሥልጣንና በጥቅም የተነሳ በተጣሉ የአንድ ፖለቲካ እምነት ተከታይ በሆኑ ጎሰኛ ቡድኖች በወያኔና በኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግና መካከል ጦርነቱ አገርሽቶ የሁለቱም ጠላት ተደርጎ በሚቆጠረው በኢትዮጵያዊነት ጎራ በተሰለፈው ሕዝብ በተለይም በአማራውና በአፋሩ ማህበረሰብ ላይ ዳግም ውድመትና ጭፍጨፋ በመካሄድ ላይ ነው።ይህ ሁኔታ ሊከሰት እንደሚችል በእኛም ሆነ በሌሎቹ አገር ወዳዶች በኩል ይሰጥ የነበረውን ማሳሰቢያና ጥሪ ለማዳመጥና በጊዜው እርምጃ ለመውሰድ ያልቻለው የጥቃቱ ሰለባ መሆኑን ታዝበናል፤ አሁንም ለከፍተኛ ጥቃት ተጋልጦ ይገኛል።

ሕዝቡ ሊገነዘብ ያልቻለው ቢኖር የነዚህ ሁለት አገር አጥፊ ሃይሎች ዓላማ በኢትዮጵያ ጥቅም ላይ ባተኮረ ጥያቄ የተነሳ ሳይሆን ኢትዮጵያን በማፍረስ ሁለቱም የራሳችን አገር ብለው ለሚመሠርቱት የወደፊት አገር ሊሆን ይገባዋል በሚሉት የመሬትና የሃብት ድርሻ ላይ የተነሳ መሆኑን ነው።ወያኔ ከወሎ የራያና አዘቦን፣ከጎንደር ወልቃይትና ጠገዴን ለም መሬቶች በመያዝ ከዚያም በሱዳን በኩል ከውጭው ዓለም ጋር ለመገናኘት ከሚችልበት ደረጃ ላይ ደርሶ ትግራይ የምትባል ነጻ አገር ለመመሥረት ሲሆን፣ከቻለም የኤርትራን ደጋ መሬት ተቆጣጥሮ ትግራይ ትግርኛ በሚለው ቅዠቱ ሁሉንም የኤርትራ መሬትና ወደቦች ተቆጣጥሮ የትልቋ ትግራይ ባለቤት ለመሆን ነው።የኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግና ደግሞ የደቡብ ወሎን፣የምዕራብ ኢትዮጵያን እስከቤንሻንጉል ድረስ ያለውን ሰፊ መሬት በመያዝ፣በምስራቁም በኩል እስከ አፋርና ሶማሌ ክልል ድረስ ያለውን በመጠቅለል፣ከደቡቡም እንዲሁ

ኩታ ገጠም መሬቶችን ብቻም ሳይሆን ተበጣጥሰው ለብቻቸው የሚኖሩ አካባቢዎችን ጭምር ሰልቅጦ ዋና ከተማዋን አዲስ አበባን ጭምር በመንጠቅ ኦሮሚያ የተባለ አገር መመሥረት ነው።ይህ ከሰላሳ ሁለት ዓመት በፊት በኤርትራ በረሃ ውስጥ በነበሩበት ወቅት ተነጋግረው የተስማሙበት የጋራ አቋማቸው ነው።በመሃሉ እንቅፋት የሚሆንባቸውን ኢትዮጵያዊ በተለይም አማራውን ማዳከምና ማጥፋት የዓላማቸው መዳረሻ አድርገው ያስቀመጡት ቅድመ ሁኔታ ነበር፤አሁንም ነው።ላለፉት 31 ዓመትም ሥልጣኑን ከተቆጣጠሩ በኋላ በተግባር የገለጹት ይህንኑ የጫካ ስምምነታቸውን ነው።

ለሃያ ሰባት ዓመታት በአንድ ኢሕአዴግ በሚል መጠሪያ ይንቀሳቀሱ የነበሩት የጥፋት ስብስቦች ያሰፈኑት ሥርዓት ከአራት ዓመት በፊት በሕዝብ እምቢባይነት ሲንገጫገጭ በመካከላቸው በተፈጠረባቸው ስጋት የተነሳ እርስ በርሳቸው ተካክደው ወያኔ ወደ መቀሌ ሲፈረጥጥ ሌሎቹ በኦሕዴድ በተባለው የኦነግ ቅርንጫፍ መሪነት ያገሪቱን ሥልጣን ተቆጣጠሩ።ለሁለቱም ተረኞች በአሽከርነት ሲያገለግል የነበረው በአማራው ስም የተሰዬመው ብአዴን የተባለው የሆዳሞች ስብስብ በያዘው ሙያ ቀጠለበት።ይህ የሥልጣን መነጣጠቅ፣የጥቅም ጉዳይ በመሆኑ ለጦርነት አሰለፋቸው፤ ከአንድም ጊዜ በላይ ተደጋጋሚ ጦርነቶች ተካሂደው ለብዙ ዜጋ ህይወት መጥፋት ምክንያት ሆነ። ባለፉት ተደጋጋሚ ጦርነቶች ኦሕዴድ መራሹ ብልጽግና በሁለት ስለት ወያኔንና አማራውን ለመምታት ዕድል አገኘ። የወያኔ ጦር ተንኮታኩቶ መሪዎቹም በቁጥጥር ስር ሲወድቁና የቀሩትም በዬዋሻው ሲርመሰመሱ የመጨረሻውን በትር ከማሳረፍ ይልቅ፣የአማራው መነሳሳትና የውጊያ ችሎታውን በማዬት ስላሰጋው ወያኔ እንደገና እንዲያንሰራራ ስውር ድጋፉን ከመሳሪያ ጭምር እዬሰጠ የለቀቀውን የመቀሌ ከተማን መልሶ እንዲቆጣጠርና ሃይሉን አሰባስቦና ይበልጥ ተጠናክሮ የአማራውንና የአፋሩን መኖሪያ ወሮ እንዲያጠቃ አጋርነቱን በገሃድ አሳዬ።በዚህ የሞራል መነቃቃት ያደረበት ወያኔ እዬከበበ እስከደብረብርሃን ድረስ ዘልቆ ብዙ ውድመትና ጭፍጨፋ እንዲፈጽም ዕድሉን አገኘ።በጉዞው ከቀጠለ አዲስ አበባ ገብቶ ሥልጣኑን እንዳይነጠቅ የሰጋው ኦሕዴድ፣የአማራውን መዳከምና መድቀቅ ካረጋገጠ በኋላ፣ ለዝቡን የድረሱልኝ ጥሪ አቅርቦ በተከፈለው የሕይወት ዋጋ ሥልጣኑን ለማዳን ቻለ።ሆኖም ግን ጦርነቱ ሊቆም አልቻለም።ምክንያቱም ሁለቱም የሚፈልጉትን ኢትዮጵያን አፈራርሶ የአገር ባለቤት የመሆኑ ዓላማ በቀላሉ ሊሳካ አለመቻሉ ነው።

እንደ መጀመሪያው ሁሉ አሁንም በተመሳሳይ ደረጃ ሕዝቡ እንዳይታገል መሰናክሎችን በመፍጠርና ሊያደራጁ ይችላሉ የተባሉትን ቀድሞ በማሳደድና በእስር ቤት በማጎር ለወያኔ መግቢያ መንገዱን ጠርጎለት ብዙ ቦታዎችን እንዲቆጣጠር አድርጓል።ለይምሰል አልፎ አልፎ በጦርነቱ የተካፈለ ቢመስልም፣ስልታዊ ማፈግፈግ በሚል ፈሊጥ መሣሪያውን ጥሎ በመፈርጠጥ ትጥቅና መሬቱን ለወያኔ ወራሪ ሃይል አሳልፎ በመስጠት ሕዝቡን ለዳግኛ ጥቃት አጋልጦታል።የመዋጋት ብቃትና ሞራል ባይኖረው እንኳን ሊዋጉና እራሳቸውን ከጥቃት ለማዳን ለሚሹት ወገኖች ትጥቁን ቢሰጣቸው በተገባ ነበር።ግን የጋራ ዓላማ ሆነና ያንን ከማድረግ ይልቅ አጋፍጦ መሸሹን መርጧል።በዚህም መከረኛው የወሎና የአፋር ሕዝብ ለተደጋጋሚ ጊዜ የመከራው ገፈት ቀማሽ ሆኗል።በስካር መንፈስ ለሚነዳው የወያኔ ወራሪ ሃይል የዘረፋና የግድያ ሱስ መወጫ ሆኗል።

ቅጥረኛ ወሬ አናፋሾች ዘግናኙን የጦርነቱን መልክና ሂደት ለቀጠራቸው የብልጽግና ቡድን በሚመች መልኩ በመንዛት የሕዝቡን ስቃይና መከራ እንደ ኳስ ጨዋታ ገባ ወጣ እያሉ ሲጫወቱበት መስማት አድርባይነት ምን ያህል ኢሰብአዊ ስሜት እንደሚፈጥር ታዝበናል።የወያኔ ጦር ከውስጥና ከውጭ በሚያገኘው ድጋፍ ተከዜን አልፎ ካለፈው ጊዜ በበለጠ ፍጥነት የጥቃት ቀጠናውን በማስፋት ግድያና ዘረፋ ሲፈጽም የሚከላከልለት የመንግሥት ሃይል ባለመኖሩ ግራ ሲገባውና ሲጨንቀው፣ለመከላከልም አቅም ሲያጣ ህይወቱን ለማዳን በዬአቅጣጫው ለመሰደድ ተገዷል።የወያኔ መንጋ በየደረሰበት ሞሰብ

እዬገለበጠ መብላትና የተሰጣ ካልሲና የሕጻን ልጅ የቅዘን ጨርቅ ሳይቀር እዬዘረፈ መሄዱ ካለፈው ጊዜ የበለጠ የችግሩን ከፍታና የዕብደት ጣራውን ያሳያል።የራበው ሕዝብ እውር ነው፤የራበው ሕዝብ የማስተዋል አቅም የለውም።የትግራይ ሕዝብ እንዲህ ሆኖ ማዬት በራሱ ለሁሉም ኢትዮጵያዊ ሃፍረት ነው።የትግራይ ሕዝብ የሚከተላቸው ጨካኞች ላለፉት 32 ዓመታት ከስደትና ከችግር እንዳላወጡት ሁሉ ለወደፊቱም እንደማያወጡት ሊያውቀው ይገባል።በነጻነት በፈለገበት ያገሩ መሬት ኖሮ ሠርቶ እንዳይበላ ከሁሉም ጋር እንዲጣላ ያደረጉትና በነጠላ እስረኛነት ቀፍድደው የያዙት መሪህ ነን የሚሉት በጭፍንም ሆነ በግዳጅ የሚከተላቸው መናጢዎች መሆናቸውን ከሚደርስበት መከራና ውድቀት ሊማር ይገባል።የነጮቹም ጫጫታ በራሱ አገር ላይ እንዲዘምትና ነጻነቱንና የአገር ባለቤትነቱን ለማሳጣት እንደሆነ ሊያውቀው ይገባል።ከባዕድ የጎረሱት በሶ ይወጣል ደም ጎርሶ ነውና ከባዕዳን በማገኘው ያልፍልኛል ወይም ዘላለማዊ መብቴን አስከብራለሁ ብሎ እምነት ሊያድርበት አይገባም። ይልቁንስ ለዘመናት አብሮ ከኖረውና ሥርወመንግሥት ከመሠረተው አማራና ሌላው ኢትዮጵያዊ ጋር ተስማምቶ መኖሩ ከሁሉም በላይ የተሻለ ነው።

የአማራው ሕዝብ በበኩሉ ባለበት ተደራጅቶ የመጣበትን አደጋ ለመቋቋም እንዳይችል  ምልክትና አርአያ ሊሆኑ የሚገባቸው ባለሥልጣኖች አሁንም የሽሽት ፊትአውራሪዎች ሆነዋል።ታዲያ ሕዝቡ ማንን አይቶ ይከተል?ጥቂቱ ከፋኖ ጋር ሆኖ የበኩሉን ድርሻ እዬተወጣ ሲሆን ሴቶችም ስንቅ እያዘጋጁ ጦር ግንባር ድረስ በመሄድ የበኩላቸውን እያደረጉ ነው።ፋኖዎቹ ድል ሲያደርጉና ወያኔ ላይ ከባድ ቅጣት ሲደርስ መከላከያ ባደረገው ተጋድሎ  የተገኘ ውጤት እንደሆነ ተደርጎ በተከፋይ  ጋዜጠኞች ጉሮ ወሸባዬ ይደለቃል።ቆቦና አካባቢዋን አልፎ ወልድያን በመከበብ  በከባድ መሣሪያ ተኩስ የታገዘ የሰው መንጋ ከተማዋን ለመያዝ ሲቃረብ የዚያ ተቃራኒ የሆነ በኦሕዴድ ውታፍ ነቃይ ጋዜጠኞች በኩል የድል ብሥራት ይናፈሳል።ሕዝባዊ ጦሩ በተለይም ፋኖና ልዩ ሃይሉ ለአገሩ ባለው ፍቅር የተነሳ በራሱ ትጥቅና ስንቅ በግንባር ቀደም የጦር ግንባር በመሰለፍ የወያኔን እርምጃ ለመግታትና ቦታዎችን መልሶ በመቆጣጠር እንደቻለ ከቦታው  የሚወጡ መረጃዎች ቢያረጋግጡም ይህንን ድል የመከላከያ ተብዬው መሪዎች  በነሱ የአመራር ብቃት የተገኘ ነው በማለት ሲኩራሩበት ይሰማል።እንደ እውነቱ ከሆነ ወያኔ ሲገፋ እግሬ አውጭኝ፣ወያኔ ሲያፈገፍግ ዘራፍ ማለትና የድል ሽሚያ ማድረግ በመከላከያ መሪዎች የተለመደ ድራማ ሆኗል።።

በሁሉም የጦር ግንባር በዋናነት የሚፋለመው የአማራው ፋኖና ልዩ ሃይል እንዲሁም የአፋር ልዩ ሃይል ብቻ ነው።የአገሪቱ መከላከያ ተብዬው አልፎ አልፎ በጦር አውሮፕላን ጥቃት አደረስኩ ቢልም የወያኔን ወረራ ሊያስቆም አልቻለም።ለማስቆምም ፍላጎት የለውም።ምክንያቱም መከላከያው የኦነግ ክንፍ በሆነው ኦሕዴድ መዳፍ ስር የዋለ ስለሆነ በአማራውና በአፋሩ ላይ የሚደርሰው ጥቃት ለሱም መልካም ዕድል ሆኖ ይሰማዋል እና ነው።ጠንካራ አማራና ኢትዮጵያዊነት፣ለወያኔም ሆነ ለኦነግ ኦሕዴድም የማይዋጥ መራራ ኪኒን ነው። የኢትዮጵያዊነት ሃይሉ ከጠነከረ ነገ ወደ ራሱ ሊመጣ ስለሚችል ከጅምሩ ሃይሉን ለመስበር  ሁኔታውን ይጠቀምበታል።የኦነግ ኦሕዴድ ጎራ ከወያኔ ጋር የጥቅምና የሥልጣን እንጂ ኢትዮጵያን በማፈራረሱ የዓላማ ልዮነት የላቸውም የሚባለውም ለዚያ ነው።

አብይ አህመድ ቆቦ ላይ ያለውን የመከላከያ ጦር ለመምራት ወልድያ ገባ የተባለው ዜና ከብዙሃን ጆሮ ሳይደርስ ከመቅጽበት አልጀሪያ ገብቶ በአገሪቱ የሰማዕታት መታሰቢያ ሐውልት ስር የአበባ ጉንጉን አስቀመጠ የሚል ዜና ስንሰማ ከምን ጊዜው ጦርነቱን መርቶና ግዳጁን አጠናቆ ለአልጀሪያ ጉዞ በቃ የሚለው መልስ ያላገኘንለትን ጥያቄ እንድናነሳ ተገደናል።የወልድያን ጉዞ ማስቀደሙም አገር በዚህ ሁኔታ እያለች ለምን ይወጣል የሚለውን ነቀፌታ ለመቀልበስ ታስቦ የተዘጋጀ ቅድመ መከላከል

እንደሚሆን ከፍተኛ ጥርጣሬ አድሮብናል።መሄዱንም የሚያሳይ መረጃ ባለማግኘታችን ከነጭራሹ ብቅ አላለም ለማለት እንደፍራለን።

ግራም ነፈሰ ቀኝ ምንም ችግር  እንደሌለባት ፈረንሳይ አገር መሪ እንደ አማኑኤል ማክሮን አልጀሪያን ለመጎብኘት መሄዱን የሚያሳይ ስዕላዊ ማስረጃ በማዬታችን  መሄዱ ባይካድም፣ለምን ሄደ የሚለውን ጥያቄ አንስቶ መተቸት ተገቢ ይመስለናል።አዎ ሄዷል፤የጉዞው ምክንያት ግን የሚከተለው ሳይሆን አይቀርም እንላለን።

አልጀሪያ መሣሪያ በመሸመት ከአፍሪካ አገሮች ቀዳሚውን ቦታ ትይዛለች።ከዚያም በተረፈ ከሩስያና ቻይና ጋር በጥምረት በአገሯ ላይ የመሣሪያ ፋብሪካ በማቋቋም ከራሷ አልፋ ለሌሎች አገራት መሸጥ የቻለች አገር ሆናለች።ይህች አገር የፈረንሳይ ቅኝ ግዛት የነበረች ሲሆን ከፈረንሳይ ጋር የጠበቀ የቋንቋ፣ የባህል፣የኤኮኖሚና የፖለቲካ ትስስር አላት።ሕዝቧ የሚግባባው ከአረብኛ ይበልጥ በፈረንሳይ ቋንቋ ነው።አብይ አህመድ ከመድረሱ ከሁለት ቀናት በፊት የፈረንሳዩ ፕሬዚደንት ማክሮን አገሪቱን ጎብኝቶ በሰማዕታቱ መታሰቢያ ስር የአበባ ጉንጉን አስቀምጧል።የአብይ አህመድን ጉዞ ምናልባትም ከዚሁ ከፈረንሳዩ ፕሬዚደንት ጉዞ ጋር የተያያዘ ጉዳይ ሳይኖረው እንዳልቀረ ለመጠርጠር ተገደናል።ያም ቀደም ሲል አብይ አህመድ ከፈረንሳይ ጋር የመሣሪያ ሽያጭ ውል ተዋውሎ ግን በምዕራባውያኑ ጫና የተነሳ ፈረንሳይ በማፈግፈጓ ሊቋረጥ ችሎ ነበር።ያንን የሽያጭ ውል እንደገና እንዲያንሰራራ ከአውሮፓ አገሮች ጀርባ ፈረንሳይ በአልጀሪያ  በኩል ለመፈጸም ያደረገችው አሻጥር ሳይሆን አይቀርም ወይም በአልጀሪያ የሚመረቱትን የጦር መሣሪያዎች ለመግዛት ነው የሚለው ግምታችን  ሚዛኑን ይደፋል ብለን እናምናለን።በሌላም በኩል አልጀሪያ ከኤርትራ ጋር የነበረውን የድንበር ውዝግብ በማሸማገሉ ልማድ ያላት አገር በመሆኗ አሁንም ከወያኔ ጋር ያለውን  ችግር እንድታሸማግል ለመጠዬቅ ይሆናል የሚል ወሬ ይነፍሳል።ሌላው ጥርጣሬ አልጀሪያ ለሚመጣው ዓመት የአረብ ሊግ ሊቀመንበርነቱን ቦታ ትይዛለች የሚለውን ተከትሎ በአባይ ግድብ ዙሪያ ከግብጽ ጋር ያለውን ንትርክ እንድታማልድ ለመጠዬቅ ነው ያሉም አልጠፉም።በግድቡ ዙሪያ በሁሉም የሊጉ አባል አገራት የግብጽ አቋም የተደገፈ ስለሆነ አልጄሪያ ሊቀመንበር ብትሆን ታስለውጠዋለች የሚለው ግምት ውሃ አይቋጥርም። ከግድቡም በፊት ሌላ ብዙ ዘመናት የተሻገሩ ልዩነቶችና  ጥያቄዎች አሉ። የኢትዮጵያን መብትና ነጻነት ለማስከበር የአረብ አገር ድጋፍ ማሳደድ ሳይሆን የሚያዋጣው ኢትዮጵያን በጠንካራ መሠረት ላይ ማለትም በኤኮኖሚ፣በፖለቲካ፣በሚሊታሪ መስክ ሲሆን በልጣ አለያም ተግደርዳሪ ሃይል  ለመሆን ስትችል ብቻ ነው።ለዚያም እንድትበቃ  አንድነቷን የሚፈታተን፣የውጭ ጠላቶቿ ሰርገው ሊገቡ የሚችሉበትን የልዩነት ምክንያት የሆነውን የጎሳ ፖለቲካና ሥርዓት ስታስወግድ ብቻ ነው።ይህ ሳይሆን ከቀረ ጠላት ሳይወራት በራሷ ተንገጫግጫ የምትበታተን አገር መሆኗ የማይቀር ዕድሏ ይሆናል።ስጋታችንም ይኸው ነው።

ኢትዮጵያን የሚያህል ባለታሪክ ነጻ ሆና የኖረች አገር በቅኝ ግዛትነት ሲረገጡ ከነበሩት ያፍሪካ አገሮች ከአልጀሪያ፣ከግብጽና ሱዳን ከሌሎቹም አንሳና ኮስሳ በዬመስኩ ተዋርዳ ጥገኛ ስትሆን፣ማዬቱ ብቻ ሳይሆን የውስጥ አንድነቷን አጥታ ለኋላ ቀር ለሆነው የጎሳ ፖለቲካ መጋለጧ ለዜጎቿ ብቻ ሳይሆን ለዬአገራቱ የአንድነት ሃይሎች በሙሉ ትልቅ የሞራል ስብራትና አገር ለመበታተን ለሚሹ ሁሉ የሞራል ድጋፍ ነው።ለአንድ አገር ትልቁ መሣሪያ የሕዝቡ አንድነት ነው።አንድነት የሌለው አገር ኑክሌር ቢታጠቅ የራሱ መጥፊያ ይሆናል እንጂ የሚያስከብረው አይሆንም።መሣሪያ ቢሰበስቡት አጠቃቀሙን ካላወቁበት ወይም ባረባና እራስን ለማጥፋት በታቀደ በእርስ በርስ ጦር ሜዳ ላይ ከዋሉት ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል።የሰላም ባለቤት የሆነ አገር የእውቀትና የእድገት ባለቤት ይሆናል።የዚያም ባለቤት የሆነ በሌሎች አገሮች የተከበረና የተወደደ ይሆናል።የሚሻውን የሚያመርት እንጂ በግዢ ዕዳ ውስጥ

አይነከርም።ላለፉት 32 ዓመታት በሰፈነው የጎሰኞች ሥርዓት በተስፋፋው የእርስ በርስ እልቂት በተከሰተው ዘረፋና ውድመት ጥላቻ እንጂ እድገትና ሰላም ብሎም አንድነት አልመጣም።የጭንቅላትን ሥራ ጉልበት ከወሰደው ፍጻሜው ውድመት ይሆናል፤ጦርነትንማሸነፍ የሚቻለው በመሣሪያ ብቻ ሳይሆን በሃሳብ ነው፣ሃሳቢዎችና ሃሳብ ካለ ብዙ ወታደር ማሰለፍና የጦር መሣሪያ ማግበስበስ አስፈላጊ አይሆንም።

የወደፊቱን ሳይሆን ያለፈውን የጦር መሣሪያ ለመግዛት የወጣውን ገንዘብ ብድር ለመክፈል ያገራችን አቅም አይፈቅድም።በአንድ ጎሳ የበላይ አዛዦች የሚመራ፣ በጎሳ ተዋረድ የተደራጀ መከላከያ አገራችንን ከውጭ ጠላት ለመከላከል ፍላጎት እንደሌለውና አለመቻሉን በሁመራና በጋምቤላ በኩል ሰርገው ገብተው ሰፊ መሬት የያዙትን የሱዳን ወራሪዎች ማዬቱ በቂ ነው።ሌሎቹም እንዲሁ ድንበር እዬጣሱ መሬት ቢቀሙ ተዋግቶ ያስመልሳል የሚል እምነት የለንም።ያባትህ ቤት ሲዘረፍ አብረህ ዝረፍ ብሎ በዬጎሳው የራሱን ድርሻ ከመቀራመት ባለፈ በኢትዮጵያዊነት ብሔራዊ ግዳጁን የሚፈጽምበት ተከለሰውነት ይኖረዋል ተብሎ አይታማም።ከውጭ ወራሪ ጋር ከመዋጋት ይልቅ ለእኩልነትና ለአገር አንድነት የሚታገሉትን ማሳደድ ተግባሩ መሆኑን በተደጋጋሚ አሳይቷል።

በጣም የሚገርመው ነገር አብይ አህመድ ስለጦርነቱ የሰጠው ማብራሪያ ነው።እንደሚታወሰው በመጀመሪያው ጦርነት የወያኔ መሪዎች በኮንቮይ ሲንቀሳቀሱ በአውሮፕላን ተመትተው ዶጋ አመድ ሆኑ የሚል ነጭ ወሬ በውታፍ ነቃይ ጋዜጠኞቹ በኩል እንዲናፈስ ካደረገ በኋላ ቀጥሎም ዋሻ ለዋሻ ሲርመሰመሱ በመረጃና ክትትል ቢሮ(Observation Room) ውስጥ ሆነን እናያቸው ነበር፤ለማጥቃት ያልፈለግነው ምርኮኞች፣ ህጻናትና ሴቶች አብረዋቸው ስለነበሩ በማዘን ነው ብሎ ነበር።አሁን ደግሞ ከሱዳን መሣሪያ ጭና የመጣችውን አውሮፕላን በሚመለከተው ዙሪያ ከሦስት በላይ እርስ በርሱ የሚቃረን ወሬ መነዛቱ ሲገርመን ስለዚያም አብይ አህመድ ጋዜጠኞች ባይነግሩንም አውሮፕላኖቹ ጨለማ ለብሰው ሲሽሎኮለኩ በካሜራ እናያቸው ነበር ብሏል።ታዲያ ካያችኋቸው ለምን ድንበር ከመሻገራቸው በፊት እርምጃ አልወሰዳችሁም በማለት ደፍሮ የጠዬቀ የለም። በአብይ አህመድ በኩል የኢትዮጵያ ሕዝብ የማስታወስ ችግር ስላለበት ካለፈው ውሸቱ ጋር የሚያስተሳስርና የሚታዘበኝ አይኖርም ብሎ ይሆናል።እኛ ግን በማስታወስ የውሸት ኮሮጆውን ዘርግፈን ከማሳዬት ወደኋላ አንልም። የሚገርመው ደግሞ ጋዜጠኞችን አልነገሩንም በማለት የራሱን የደህንነትና መረጃ ተግባር ለጋዜጠኞች አሳልፎ መስጠቱና መውቀሱ ነው።

ከጥፋት ሃይሎቹ ጎን የተሰለፉት የምዕራባውያን መንግሥታት እንደልማዳቸው በአሁኑም ጦርነት ሰልፋቸውን በግልጽ አሳይተዋል።ከዲፕሎማሲ ድጋፍ በተጨማሪ በተቸገሩት ወገኖቻችን ስም በሚገባ የእህልና መድሃኒት እርዳታ ስምና ሽፋን ለወያኔ ተዋጊ ቡድን መሣሪያ ማቅረባቸውን ቀጥለውበታል። ወያኔ ያሸነፈ ሲመስላቸው ድምጻቸውን ለዘብ በማድረግ እርዳታ እርዳታ ሲሉ፣ወያኔ በጦር ሜዳ የተሸነፈ ሲመስላቸው ደግሞ የሰላም አባት በመምሰል ጦርነቱ ይቁም፣የሰላም ድርድሩ ይቀጥል ይላሉ። ለእነሱ ሰላም ማለት ጥቅማቸው የሚከበርበት ሁኔታ ይፈጠር ማለታቸው እንጂ ኢትዮጵያ ተረጋግታ የምትቀጥልበት፣ ለጦርነት የተሰለፉትና የቀሰቀሱት ወንጀለኞች ለፍርድ መቅረባቸው አይደለም።

አገራችን ላለችበት ቀውስና የእርስ በርስ እልቂት መፍትሔው የጦርነት ሰለባ የሆነው ሕዝቡ ነው።አንዱ ሌላውን ገሎ የሚያገኘው ጥቅም እንደማይኖረው ተረድቶ ለጦርነት ያበቃውን ምክንያትና የጦርነት ነጋሪት ጎሳሚ የሆኑትን የጥፋት ሃይሎች መንጥሮ በማውጣት ማሶገድ ይኖርበታል።በስሙ የሚነግዱ ከይሲዎች ለራሳቸው ጥቅም እንጂ ለሕዝቡ እንዳልቆሙ ባለፉት 32 ዓመታት የሥልጣን ዕድሜያቸው አሳይተዋል።ስለሆነም ለእኔ ጥቅምና መብት ነው የሚታገሉት ብሎ እራስን ማታለልና ለእልቂት መሰለፍ ተገቢ አይደለም።ትውልድ በጥላቻና በቂም በቀል እንዲኖር ከማድረግ ባለፈም

የአንድ ትልቅ አገር ባለቤትነትን ያሳጣል።ጠባብ ጭንቅላት የጠባብ መሬት እስረኛ ማድረጉን በክልሎች አይተነዋል።ከዚያ ለመውጣት ሁሉም እምቢ ብሎ እጅ ለእጅ ተያይዞ መነሳት አለበት የሚለውን የዘወትር ጥሪ አሁንም እንደግማለን።

ሰፊው ሕዝብ በተመሳሳይ የድህነት ኑሮ ውስጥ የሚኖር ነው።የተንደላቀቀ ኑሮ የሚኖሩት በስሙ ሥልጣን ላይ የተቀመጡት ፣ከመሃሉ የወጡት ጥቂቶቹ ብቻ ናቸው።የትግሬውም ሆነ የኦሮሞው፣ የአፋሩም ሆነ የአማራው፣የሲዳማም ሆነ የሶማሌው፣የጋምቤላውም ሆነ የሐረሪው ፣ሌላ ሌላውም ሰፊ ሕዝብ አንዱ ከሌላው የሚሻል ኑሮ ደረጃ የለውም።ሁሉም በድህነትና በመከራ የሚኖር ሕዝብ ነው። ያንዱ መወገድ ወይም ማለቅ ለሌላው ይበልጥ ለባሰ ድህነትና እልቂት ይዳርገዋል እንጂ ብሩህ ተስፋና የተሻለ ኑሮ ይዞለት አይመጣም።ለተሻለ ህይወት እንዲበቃ መከራ ውስጥ እንዲገባ ያደረጉትን በስሙ የሚነግዱትን እራስ ወዳዶችና የዘረጉትን የከፋፍለህ ግዛ  የጎሰኝነት ሥርዓት ማሶገድ ነው።

በመጨረሻ ልናሳስብ የምንወደው ይህ ጦርነት እንዳለፈው ጊዜ ቢቆም ጭራሽ ጦርነት ተወገደ፣ሰላምና አንድነት ሰፈነ ማለት አይደለም።የጦርነት ምክንያቱ ካልተወገደ ለቀጣዩ ጦርነት የመዘጋጃ ጊዜ መፍጠር ይሆናል።ወያኔና ኦነግ-ኦሕዴድና መሰሎቻቸው እስካሉ ድረስ ጦርነት አይቀሬ ነው።በጊዜያዊ "ድል"መመርቀንና መዘናጋት ተገቢ አይደለም።በተለይም የአማራው ፋኖና ልዩ ሃይል እንዳለፈው ጊዜ የኦሕዴድ ሰለባ ላለመሆን እራሱን መጠበቅ ይኖርበታል።በአንድ የጦር ሜዳ ላይ አብሬ ውያለሁ ብሎ በመዘናጋት ልቡንም ትጥቁንም አሳልፎ መስጠት አይኖርበትም።ከጦርነቱ በኋላ እንደ ባዶ ካዝና ወይም ቀለህ እንደሚወረውሩት ልብ ይበል።በወለጋና በሌሎቹ ቦታዎች የሚጨፈጨፉትን ወገኖቹን እያሰበ የሱም እጣ ፈንታ ከዚያ እንደማይለይ ተገንዝቦ እራሱን ችሎ ለመቆም ዝግጁ ሊሆን ይገባል፣የተነሳበትን ዓላማ ሊዘነጋው አይገባም።የአዲስ አበባንም የመዋጥ ሂደት እያሰበ እኔም ልዋጥ እችላለሁ ብሎ ማሰብ ይኖርበታል። ኦሕዴድ ከወያኔ የተሻለ አጋሩ ሊሆን እንደማይችል ሊያውቀው ይገባል። በአብይ አህመድ የሚፈልጉትን እያሳዩህ ወደምትፈልገው ንዳቸው የሚለውን ህሳቤ ተገንዝቦ በጀግና ስም ለሚሰጠው ሹመትና ሽልማት ዶሮን ሲያታልሏት በመጫኛ ጣሏት እንዳይሆንና ተጠልፎ ላለመውደቅ ነቅቶ መጠበቅ ተገቢና አስተዋይነት ነው።ድርጅታዊ መዋቅሩን ማስፋትና  ማሳደግ እንጂ ማመንመን አይጠበቅበትም።ያልጠረጠረ ተመነጠረ!

ትግሉ የጎሰኞች ሥርዓትና የዘረጉት የክልል አወቃቀር እስኪፈርስ፣የሚመሩበት የጎሳ ሕገ ጥፋት በእውነተኛ ኢትዮጵያዊነትን በሚያንጸባርቅና በሚያስከብር ሕገ-መንግሥት እስኪቀዬርና  ብሎም በሕዝቡ ምርጫና ፍላጎት ከጎሰኝነትና ከሃይማኖት የጸዳ ለሁሉም፣የሁሉም በሁሉም የሆነ ሕዝባዊ መንግሥት እስኪፈጠር ድረስ መሆን አለበት።

ከወያኔ ጋር የሚደረገው ጦርነት የሁሉንም ቀልብ ወደ ሰሜኑ ሲያዞር በኦነግ ኦሕዴድ የሚካሄደው የአማራው ጭፍጨፋ በገዘፈ መልኩ በምዕራብ ኢትዮጵያ በተለይም በወለጋ ውስጥ ተጠናክሮ ቀጥሏል።በመንግሥት ተብዬው መጠበቅ የነበረባቸው ባንኮችም እንዲዘረፉ የክልሉ ባለሥልጣኖች የይለፍ ፈቃድ ሰጥተው ተባባሪ ሆነዋል።በሸዋ ሮቢት የሚኖሩትን አማራዎች ፋኖና ሚሊሽያ በማለት ከቦ መግደልም የሰሞኑ አሰቃቂ  ድርጊት ሆኗል።

ፊታችንን ወደ ኢትዮጵያ አዬር መንገድ ስንመልስ ደግሞ የዓለም ትልልቅ አዬር መንገዶች በኪሳራ ለመኖር ላለመኖር ፈተና ውስጥ ገብተው በሚዋዥቁበት ጊዜ የአገራችን አዬር መንገድ በአንድ ዓመት የበረራ አገልግሎቱ  የተጣራ ከአንድ ቢሊዮን ዶላር ያላነሰ ትርፍ ማግኘቱ ይፋ ሆኗል።ማትረፉ ደስ ቢለንም ትርፉ እንዳለፉት ጊዜያቶች ሁሉ  የት እንደሚገባ ስለማይታወቅና  የኦነግ ኦሕዴድ መራሹን መንግሥት የፕራይቬታይዜሽን አካሄድ ከግምት ውስጥ ስናስገባ ምናልባትም ለጨረታ ተሳታፊዎች

የመሳቢያ ፕሮፓጋንዳ ሳይሆን አይቀርም የሚል ጥርጣሬ አድሮብናል።ሊበሉ ያሰቧትን አሞራ ይሏታል ጅግራ እንደሚሉት ሆኖብናል።ለሽያጭ ከቀረበም አንዱ ተጫራች የኦሮሙማው ቡድን ያዘጋጀው የምሥራቅ አፍሪካ አዬር መንገድ ይሆንና በኢትዮጵያ ገንዘብ የኢትዮጵያን አዬር መንገድ ወስዶ በምስራቅ አፍሪካ አዬር መንገድነት አለያም የኋላ ኋላ የኦሮሚያ አዬር መንገድ ብሎት ያርፋል ማለት ነው።

ወያኔና አጋሮቹ የጦርነቱ አቅጣጫ ስላላማራቸው ይዘው ብቅ ያሉት ስልት ደግሞ በጣም አስቂኝ ሆኗል።የትግሬ ሕዝብ ከአማራው ሕዝብ ጋር ጠብና ቂም በቀል የለውም፤በሰላም አብሮ የኖረና ሊኖርም የሚችል ሕዝብ ነው።ስለሆነም አንድ ላይ ሆነን ያለውን የጋራ ጠላት እናሶግድ የሚል ጨዋታ ይዘው ብቅ ብለዋል፤አሜሪካኖቹም ይህንኑ ካርታ የሚቸረችር ቡድን ወደ ኢትዮጵያ ለመላክ መዘጋጀታቸው ተሰምቷል፣ያንንም በሳማንታ ፓወል በኩል የአማራውን ክልል ጥላችሁ ውጡ የሚለው ትዕዛዟ የስልቱ መንደርደሪያና አመላካች እንደሆነ ተረድተናል።

ለመሆኑ ከአማራው ጋር በሰላም እንኖራለን ሲሉ በራያና አዘቦ፣በወልቃይትና ጠገሌ ላይ ያላቸውን ጥያቄ ጥለውት ነው ወይስ እንደተሸከሙት?በአማራውና በአፋሩ ሕዝብ ላይ ላደረሱት መጠነ ሰፊ ወንጀልና ጭፍጨፋስ ማን ተጠያቂ ነው ይላሉ? እኛም በዚች ሃረግ ጅልነታችሁን መርምሩት እንላለን።

ወትሮ ነበር እንጂ መጥኖ መደቆስ፣

አሁን ምን ያደርጋል ድስት ጥዶ ማልቀስ።

አዎ እኛም ቢሆን ሁሉም የኢትዮጵያ ሕዝብ በሰላም እንደኖረው ሁሉ ሊኖር ይችላል የሚል እምነት አለን፤የምንታገለውም ለዚያው ነው።ሆኖም ግን በሰላም እንዳይኖር ያደረጉትና ደም ያፋሰሱት ወያኔ፣ ኦነግና የኦነግ ውልዶች እንዲሁም ጸረ ኢትዮጵያ የሆኑት ቡድኖች ሁሉ  ሲጠፉና የዘረጉት የጥፋት ፖለቲካ ከነአስተሳሰባቸው ሲወገድ ብቻ ነው።

ኢትዮጵያ በአንድነትና በነጻነት ለዘለዓለም ትኑር!